# የሕግና የሕግ ተቋማትን ትምህርት ማስተማርና መማር

ሰላሙ በቀለ*

## አጀማመር (መንደርደሪያ)

ይህን ፅሁፍ ሳዘጋጅ ወደ ኋላ ተመልሼ ማስታወሻዎችን ሳገላብጥ ብዙ ትዝታ ቀሰቀሰብኝ፤ የብዙ ተማሪዎቼ ፊት ገጭ አለ፡፡ ለምሳሌ ፍፅም 20 ዓመት የሕግ ትምህርት ቤትን ትቶ፣ ብዙ ሕይወት አሳልፎ ኖሮ ኖሮ መጥቶ እንደገና ከልጅ ልጆቹ ጋር ሀ ብሎ የሕግ ትምህርት ጀምረ፡፡ «Senior Citizen» (አንጋፋ ዜጋ) እለው ነበር፡፡ ብዙ ያነበበና የሚያውቅ ስለነበረ የሚያነሳቸው ጥያቄዎችና የሚያደርገው ክርክር የጐለበተ ነበር፡፡ ከተመረቀ በኋላ በኢቴቪ ETV የእንግሊዝኛ ዜና አንባቢ ሆነ፡፡ የአበበ ባልቻ ቲያትረኛና ነጋዴ መሆን አላስደነቀኝም፡፡ ምነው ቢባል ጥብቅና ከትያትር ጋር በጣም የተቀራረበ ነው፡፡ ጥሩ ጠበቃ ጥሩ የቲያትር ተዋናይ መሆን ይችላል፡፡ ጥሩ ተዋናይ ግን ሕግ ካልተማረ ጥሩ ጠበቃ መሆን አይችልም፤ ይህ ትክክል ነው፡፡ የአበበ ነጋዴ መሆን ምንም አይገርምም፡፡ በትምርታቸው ሳቢያ ብዙ የሕግ ባለሞያዎች የተቀጣላቸው ነጋዴዎችና የኩባንያ መሪዎች ናቸው፡፡ ይህ ማስረጃ በማያስፈልገው ሁኔታ በአሜሪካ ዩኤስኤና ካናዳን ጨምሮ፣ አሁን ደግሞ ላቲን አሜሪካን ደቡብ አሜሪካን፣ ኤሮፕንና ጃፖንና አካባቢዋ ያሉትን አገራት ጨምሮ ይገኛል፡፡ፈረንጅ እንደሚለው <u>ኤማን ኦፍ አል ትሬድስ፡፡</u>

ይህስ በጄ ይሁን እግዚፍጥረታት ፈቅዶ ብዙ ተማሪዎች አስተማርኩ፡፡ አሁን ትዝ ሲሉኝና ከራሴ ጋር ብቻዬን ስጫወት እገሌ የት ይኖር ይሆን? እገሌስ ምን ይሠራ ይሆን? ሲል መንፈሴን አሳብ መንጥቆ ይወስደዋል፡፡ ይህ ማለት ሁሉም ተዋጥቶላቸዋል ማለት አይደለም፡፡ በሰው ልጅ ኑሮ ሕግና ደንብ መሠረት መውደቅ መነሳት ያለ ነው፡፡

በዚህ አርእስት ጽሑፍ ፃፍ ስባል የአርእስቱን ይዘት «ምናምንቴ» ደረቁን ከመዘገብ ይልቅ እስከዛሬ ያላወሳሁትን መግለፅ ፈለኩ፡፡

ይህን የምታነቡ ምንአልባት በሕግ ትምሕርት ሒደት አልፋችሁ ይሆናል፡፡ ከሆነ ዘመኑን አስቡት፤ እንዲሁም ተሞክሮውን፡፡ በዚህ ጽሑፍ አርእስት ጉዳይ "ላወራ" የምችለው ከራሴ ተሞክሮ በመነሳት ነው፡፡ ስለቁምነገሩ ማሰብና ማውጠንጠን የጋራችን ነው ብሎ በማመን ነው፡፡ ሕግ ያልተማራችሁ አንባቢዎች ደግሞ ከይቅርታ ጋራ የሕግ ትምሕርትን ክብደትና ችግር ተረዱልኝ፡፡

---

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሕግ ፋክልቲ ረዳት ፕሮፌሰር (የቀድሞ)

## 1. የሕግ ማስተማሪያ ዘዴ

ይህ ለዛሬው አርእስት ጥሩ መግቢያ ነው፡፡ ሳላንዛዛው በአጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

### 1.1 አገር ቤት

እኔ ተማሪ ሆኜ አስተማሪዎቻችን የተለያየ የማስተማር ዘዴ ነበራቸው፡፡ ዘዴው አንድ ዐይነት ይሁን የሚል አቋም አልነበረም፡፡ ኋላ አስተማሪ ሆኜ በወቅቱ ከነበሩት ነባር አስተማሪዎች ጋር (በተለይ ዲን ቶምሰንና ፕሮፌሰር ችቹኖቪች) ስንጫወት ስለማስተማር ዘዴ ሁልጊዜ በአካዳሚክ ኮሚሽንና በፋኩልቲ ስብሰባ የተጧጧፈ ክርክር ይደረግ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ እኔም አስተማሪ ከሆንኩ በኋላ ያከራክር ነበር፡፡ በጐ ነው ጥሩ፣ ክፉ ነው መጥፎ ውስጥ ሳልገባ አስተማሪዎቹን የሚከተለውን ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር፡፡ የእያንዳንዳቸው ዘዴ የመጡበትን በስተኋላ ሲያንፀባርቅ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ራሳቸው የተማሩበትን ዘዴ ትተው ይበጃል የሚሉትን ይጠቀሙ ነበር፡፡

ዲን ፖል ሶክራቲክ የሚባለውን ይጠቀም ነበር፡፡ ይህ ዘዴ አስተማሪው በአንድ ነጥብ ላይ መጠነኛ ማብራሪያ ይሰጥና ከዚያ እሱ ጥያቄ ይጠይቃል፤ ተማሪዎቹ ለጥያቄው መልስ እንዲሰጡ ይጋብዛል፣ ግብግብ፡፡ እንደማስታውሰው ስንጨናነቅ ትክክል የሆነና ያልሆነ መልስ ለመስጠት አትሞክሩ፣ መልስ ይሆናል የምትሉትን ከነተገቢው ምክንያት ጋር አቅርቡ ይል ነበር፡፡

ሴድለር ሶክራቲክና ሌክቸር ዘዴ ይጠቀም ነበር፡፡ የሱ ትምህርት በጣም ከባድ ነበር፡፡ ለስሙ የሥነ ሥርዐት ሕግ ይባል ነበር እንጂ በጣም የሰፌ ሰፌ ነበር፡፡ ዐይናችን ሲፈጥ ያይና ወደ ሌክቸር ዘዴ ይዛወራል፡፡

ሌውንሽቲን ኬዝ ዘዴ የሚባለውን ነበር የሚጠቀመው፡፡ ኬዝ ዘዴ የሃርቫርድ መምህራን የነበሩ ስቶንና በተለይ ላንግደን የፈበረኩት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያውን ኬዝ ደድሊንን የሚረሳ የሕግ ተማሪ ይገኛል ብዬ አላምንም፡፡ በጣም የሚደንቅ ዘዴ ነው፡፡

ችቹኖቪች ሌክቸር ብቻ ነበር የሚጠቀሙት፡፡ እንዳውም ቁራጭ ርሳሳቸው አትረሳኝም፡፡ ብዙ ጊዜ በትምርቱ ስለሚመስጡና ትምርቱንም በጣም ስለሚያውቁት ከራሳቸው ጋር ሲጫወቱ ድምፃቸው ጥፍት ይልብናል፡፡ የሚያስተምሩት እንዳይጠፋብን ድምፃቸውን ለመስማትና የሚሉትን ወፍ ስንዴ እንደምትለቅም ለመልቀም ወደሳቸው የሚቀርበውን የፊት ወንበር ለመያዝ የነበረው ሽሚያ አይረሳኝም፡፡ አንዳንድ አወቅን የሚሉና ሶክራቲክ ዘዴን አጥብቀው የሚወዱ የሳቸውን ዘዴ ሲያናንቁ ግብዞች ናችሁ እያልኩ እገስፃቸው ነበር፡፡

እስታንገር ዓለም አቀፍ ሕግ ሲያስተምር ዲስካሽን ብቻ ነበር የሚጠቀመው፡፡ ካናካቴው ብዙ ጊዜ፣ ያን ጊዜ ሬሲንግ ክለብ እሚባለው፣ ጃንሜዳ ወስዶ ቢራና ለስላሳ እየጋበዘ ነበር የሚያስተምረን፡፡ መቼስ ዮሐንስ ኀሩይ ሚስጥር አወጣህ ባይለኝ የእስታንገርንና የቶፒንግን ቢራ የጠጣው የትየ ለሌ ነው፡፡

ቸርችና ሲልኪ ሶክራቲክ፣ ዲስካሽንና ሌክቸር ዘዴዎች እየቀላቀሉ ነበር የሚጠቀሙት፡፡ ቶፒንግ ፒተር ሳንድና ኢማንኩተር አመጣጣቸው ከኢሮፕ ዩኒቨርሲቲ ትራዲሽን ስለነበር ሌክቸር ብቻ ነበር የሚጠቀሙት፡፡ ቢሆንም አልፎ አልፎ ዲስካሽን ይጋብዙ ነበር፡፡

እንግዲህ እኔ በግሌ ቀና ሆኖ ያገኘሁት ዘዴ ሶክራቲክና ዲስካሽን ነበር፡፡ ሌክቸር ለማብራሪያ ያህል ሲጥመኝ፤ ሕግን በሱ ብቻ ማስተማር የሕግ ትምህርትን ግብ እንደማይመታ ተሰማኝ፡፡ ለምን ቢባል በግሌ እንደገባኝ እነዚህ ዘዴዎች በማስማር መማሩ ሒደት አንደኛ ተማሪውን የሚያሳትፉ ሲሆን ሁለተኛ ወደፊት የሕግ ባለሞያው በግሉ እንዲያስብና ሐሳቡን እንዲገልፅ ያስተምሩታል፡፡ አክቲቭና ኢንታርአክቲቭ ያደርጉታል፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የሕግ ባለሞያ ሥልጠና አንቀጽ ጠቅሶ ማነብነብ ሳይሆን ሐሳቡን በትክክል ገልጾ፣ መፍትሔ አቅርቦ ተከራክሮ፣ አስረድቶ ማሳመን ነው፡፡ ከዚህ ወዲያ ቀላምዶ ያልሆነውን ሆነ፣ የሆነውን አልሆነም ብሎ ዘበራርቆ የሚያዘበራርቅን የሕግ ባለሞያ ለማለት ይከብደኛል፡፡

እርግጥ ተማሪዎች ሆነን ሁላችንም ከሌክቸር ዘዴ ትራድሽን የመጣን ስለነበርን ሌሎቹ ዘዴዎች ሳያደናግሩንና ራስ ምታት ሳይሰጡን አልቀሩም፡፡ ኋላ በመጠኑም ቢሆን ጥቅማቸው ሲገባን ለመራቀቅ መሞከር ቋመጠን፡፡

## 1.2 አሜሪካ

አሜሪካ አገር ሃርቫርድ ሕግ ት/ቤት ስማር ተመሳሳይ ሁኔታ ነው ያጋጠመኝ፡፡ ከትምህርቱ መክበድ በስተቀር ምንም የዘዴ ለውጥ አላገኘሁም፡፡ ትምህርቱ ደግሞ ለአሜሪካ ጉዳይ ተብሎ የተቀረፀ ስለሆነ እሱን ፏት ብሎ ማጥናቱ ብዙም ጠቀሜታ የለውም፣ በተለይ አሜሪካ አገር ተማርኩ ከማለት ውጭና እዛው ቀርቶ ለመሥራት ዕቅድ ከሌለ ፡፡

ሳክስ ሊጋል ፕሮሲስ ስያስተምር እንደ ዲንጉል ሶክራቲክ ዘዴ ብቻ ነበር የሚጠቀመው፡፡ መቼስ በጥያቄ ሲያፋጥጥ አያድርስ ነው፡፡ ትቶ አይተውም፡፡ አንዳንድ ጉበዝ ተማሪ ቢከራከረውም በመጨረሻ ያልታሰበ ጥያቄ ሲያመጣ የተማሪው ክርክር ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ ተንከባለለ ስሩ ተቆርጦ ነው፡፡ መቼስ ጉበዝ ተማሪዎች ከሱ ጋር መከራከር ደስ ይላቸዋል፡፡ እሱም ይረካል እንደኔ ያለው ግን ካሁን አሁን ጠየቀኝ ሲል ሽሽት ነው፡፡ አንድ ቀን ዓለም አቀፍ ተማሪዎች ግብዣ ተደርጎ ቢያስተዋውቁኝ፣ «አላየሁህም ምን አልባት የመጨረሻ ኋለኛው ወንበር ይሆናል የምትቀመጠው {ልክ ነው}፣ ትምህርቱን እንዴት

አገኘኸው» አለኝ «ጥሩ ነው ግን ከባድ ነው፤» ብለው፣ «ምን አልባት የማስተማሪያ መጽሐፍ ስለሌለው ነው፤ እያዘጋጀሁ ነኝ» አለኝ፡፡ ይህንን እንዲመጣ አርጌ የሕግ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነበር፡፡ መቼስ ጠፍቶ ወይም ተሰርቆ ይሆናል፡፡

ኮክስ ሌበር ሎ ሲያስተምር እንደ ሴድለር ሶክራቲክና ሌክቸር ነበር የሚጠቀመው፡፡ የተወሳሰበውን አቅልሎ ሲያቀርበው ይደንቅ ነበር፡፡ ሰውዬው በጠባዩ ረጋ ያለ ስለነበረ በሶክራቲክ ዘዴው ብዙም አያስጨንቅም፡፡ ሳቂታና ነገር አቅላይ ስለነበር ተማሪዎች እንደፈለጉ ይከራከሩታል፡፡ መጨረሻ ላይ «ትክክለኛውን ክርክር ከደረስክበት እባክህ ንገረኝ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተመሳሳይ ጉዳይ አለኝ፤» ብሎ ይዘጋል፡፡ ተማሪ ሁሉ ሆ ብሎ ይስቃል፡፡ አለባበሱና ቁመናው ዘናጭ ነው፡፡

ፍሮይንድ የሕገ መንግሥት ሕግ ያስተምር ነበር፡፡ እሱ የሕግ ት/ቤቱ ብቻ ፕሮፌሰር ሳይሆን የሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ነው፡፡ ይህ ማለት በየትኛውም የዩኒቨርስቲ ፋኩልቲ ውስጥ ማስተማር የሚችል፡፡ አብዛኞዎቹ አስተማሪዎች ከኤል ኤል ቢ ዲግሪ ሌላ የሌላቸው ሲሆኑ እሱ ብቻ ኤል ኤል ዲ ነበረው፡፡ ልክ እንደ ቼቼኖቪች ሌክቸር ነው የሚያረገው፤ እንዳውም ሁልጊዜ መጽሐፍ ይዞ ገብቶ ያን አንብቦ ሰዓቱ ሲደርስ ጠቅሶን ይወጣል፡፡ ዕውቀቱ ግን የማይደረስበት ነው፡፡ መጽሐፉን ስላላየን ከመጽሐፉ ይሁን ከተሞክሮው የሚያስተምረን መለየት አይቻልንም፡፡ ብዙ ጊዜ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ እንዲሆን ስሙ ተጠቁሞ እምቢ ያለ ሰው ነው፡፡ ኢን ዘ አይ ኦፍ ዘ ስቶርም ያለውን ስለጠቅላይ ፍ/ቤት የጻፈውን ካነበብኩ በኋላ የእምቢታው ምክንያት የገባኝ መሰለኝ፡፡

ዲን ግሪዝወልድ ታክስ ሎ ነበር የሚያስተምረው፡፡ የአሜሪካ ታክስ ሎ በጣም ውስብስብና አስቸጋሪ ነው፤ ሰፊ ከመሆኑም በላይ ዝርዝሩ ማለቂያ የለውም፡፡ የታክስ ሎ ኢክስፐርቶች እንኳ ጠቅላላውን ሳይሆን በተወሰነ ክፍል ነው ጠይቀው የሚረዱት፡፡ ለምሳሌ የኮርፖሬት ታክስ ኤክስፐርት ስለ ካፒታል ጌንስ ዕውቀቱ ውሱን ነው፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ታክስ ኤክስፐርትና የስቴት/ሚኑሲፖል ታክስ ኤክስፐርት፡፡ ታዲያ ዲን ግሪዝወልድ ያንን ተራራ ነው ፈልፍሎ ንዶ የሚያሳፍሰው፡፡ የሚጠቀመው የዲስከሽን ዘዴ ነበር፡፡

በኋላ ስታንፎርድ፣ ፖል አልቶ፣ ካሊፎርንያ ለትምህርት ሔድኩ፡፡ በዛ ወቅት በመጠኑም ቢሆን የተማሪነቱንና የአስተማሪነቱን ሒደት ስላየሁት የስታን ፎርድን የተማሪነት ዘመን በደንብ ለማጣጣም ቻልኩ፡፡ ስታንፎርድ አስተማሪዎቹ የሚጠቀሙበት ዘዴ ከኛም ሆነ ከሃርቫርድ በጣም የተለየ ነው፡፡ በብዛት ሌክቸርና ዲስካሽን ነው፡፡ ማናቸውም ሶክራቲክ ወይም ኬዝ ዘዴ አይጠቀሙም፡፡ በርተን ለምሳሌ ኢንተርናሽናል ፕራይቬት ሎ ሲያስተምር ብላክቦርድ በብዛት ይጠቀማል፡፡ እንዲህ ብሎ ነገር እኛም ዘንድ ሃርቫርድም አልነበረም፡፡ ሲ፣ ገና በ30 ዓመቱ ሙሉ ፕሮፌሰር ቴነርድ የሆነ፣ ስለቻይና ሕግ ሴሚናር ሲሰጥ የሚጠቀመው ዲስከሽን ነው፡፡ እንዳውም አርእስት ተሰጥቶን እኛ ነበር

የምናቀርበውና ዲስካስ የምናረገው፡፡ ስታንዳርድ ያሉት አስተማሪዎች ከአንድ ሁለቱ በስተቀር ሁሉም ወጣቶች ነበሩ፡፡

## 2. ማስተማር ስጀምር

ለጥቂት ዓመታት አገር ውስጥ ገቢ፣ አየር መንገድና ትምባሆ ሞኖፖል ከሠራሁ በኋላ ጠበቃ ሆንኩ፡፡ በዚያ ወቅት የሰርተፊኬት፣ ዲፕሎማና የዲግሪ (በማታና ቀን) ትምህርቶች ይሰጡ ነበር፡፡ ከነዚህ ሌላ በልዩ ፕሮግራም ለዳኞች፣ ለፖርላማ አባሎች፣ ለአስተዳደር ሰራተኞችና ለፖሊሶች ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ ሁሉንም የተጠቀሱትን አስተምሪያለሁ፡፡ የዲግሪ ተማሪዎችን ሳስተምር ሶክራቲክ ዘዴ ነበር የምጠቀመው፡፡ ሌሎቹ ግን ከዕድሜያቸው፣ ሁኔታቸውና የትምህርቱም ዓይነት ሌላ ዘዴ መጠቀም ስለማያስችል ሌክቸር ነበር የምጠቀመው፡፡ በኋላም ዲን ቶምስን አግባብቶኝ ጥብቅናውን ትቼ ሙሉ ቀን መደበኛ አስተማሪ ሆንኩ፡፡

ወደ አስራ ሶስት ያህል ትምህርቶች አስተማርኩ፡፡ በመጨረሻም ሊጋል ሒስትሪ ኮርስ እንዲኖር አካዳሚክ ኮሚሽን እንዲፈቅድ ጠይቄ ከፈቀደ በኋላ ኮርሱን ራሴ ማስተማር ጀመርኩ፡፡ በተከታታይ ዓመታት ለብዙ ዘመን ያስተማርኩት ሊጋል ሒስትሪ ነው፡፡

በነዚህ የማስተማር ረጅም ዘመንና ውጣ ውረድ መታከት ከኬዝ ዘዴ በስተቀር ሁሉንም የማስተማር ዘዴዎች ተጠቅሚያለው፡፡ የሌክቸር ዘዴን ወደኋላ ብዙም አልጠቀምበትም ነበር፡፡ ሌክቸርም ባይሆን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ብዙ ጊዜ እሰጥ ነበር፡፡

## 3. ሊጋል ሒስትሪ ትምህርት መጀመር

አንዳንድ ሰዎች የሕግ ታሪክን አስፈላጊነትና ጥቅም አያምኑበትም፡፡ ከሞያ አንፃርም የሕግ ባለሞያ መሣሪያ መጽሐፍ ውስጥ የታወጀው ሕግ ነው ይላሉ፡፡ እርግጥ ይህ መሠረታዊ ነው፤ የሕግ ትምህርት በዚህ ብቻ ከተወሰነ አስተያየትን ያጠባል፡፡ አባባሉም ፍፁም የሆነ ዩቲሊታሪያን እምነት ነው፡፡ የሕግ ሞያም የሮቦት ሥራ ይሆናል ፡፡

ታሪክ ለሕግ ፍትሐዊ አካባቢው ነው፣ አካባቢውን ያላወቀና ግምት ውስጥ ያላስገባ ከስሕተትና ጥፋት ውስጥ ይደርሳል፡፡ ታሪክን የማያቅና ያልተረዳ በታሪክ የተሰራውን ስሕተት ይደግማል ይባላል፡፡

የታሪክ ክስተቶች ለሕግ ፍትሐዊነትና የበላይነት ማስረጃና ዋስትና ናቸው፡፡ አዋጅ በፋብሪካ የሚፈበረክ ሳይሆን መጀመሪያ አለው፤ ታሪካዊ ምክንያት አለው፡፡ የሕግ እድገት ወፍ ዘራሽና ቆርጠህ ቀጣጥል ሳይሆን መሠረቱ የሕግ ታሪክና አመጣጥ ነው ፡፡

ለታሪክ ዋጋ የማይሰጡ ታሪክ የምንሠራው እኛ ብቻ ነን ብለው የሚዘብቱ ናቸው፡፡ እነሱ ከየት መጡና፣ ካላፈ ታሪክ ነዋ! የሚተካቸውስ? መጪ የወደፊት ታሪክ አይደለም፡፡

በግሌ በታሪክ የማያምኑትን በአንድ ዐይነት ቡድን እፈርጃቸዋለሁ፡፡ እነሱንም እንደየሁኔታው የሚከተሉት ጥቅሶች የሚገልፃቸው ይመስለኛል፡፡

‹‹In the eyes of empire builder's men are not men but instruments Napoleon Bonaparte›› (ለግዛት አስፋፊዎች ሰዎች ሰው ሳይሆኑ መሣሪያ ናቸው፡፡ ናፖሊዮን ቦና ፖርት)

‹‹Do not hold the delusion that your advancement is accomplished by crushing others.›› Marcus Talluis Cicero (ሌሎችን በመጨፍለቅ እኔ አድጋለው የሚል ቅዥት አትያዝ፡፡ ማርከስ ቱሊየስ ሴሲሮ፡፡)

"Men in authority will always think that criticism of their policies is dangerous." (Henry Steele Commager (ባለሥልጣኖች ፖሊሲያቸውን መንቀፍን ሁል ጊዜ አደገኛ አርገው ያስባሉ፡፡ ሔነሪ ስቲል ከማገር፡፡)

"If you are neutral in situations of injustice, you have chosen the side of the oppressor." Bishop Desmond Tutu. (በኢፍታሐዊነት ጉዳይ ገለልተኛ ከሆንክ የጨቋኙን ወገን መርጠሃል፡፡ ቢሾፕ ዴዝመንድ ቱቱ፡፡)

ከዚህ በላይ ጥቅሳቸውን የፃፍንላቸው ሰዎች በተለያዩ የታሪክ ዘመን (ከ106 ክክ ልደት በፊት እስከ 12ኛው ምዕተ ዓመት የኖሩና ቱቱ አሁንም በሕይወት ያለ ነው፡፡) ሁሉም ጥቅስ የሚያመለክተው የፍትሕ ጉዳይንና ታሪክን ስለሚዘነጉ ወገኖች ነው፡፡

## 4. የሊጋል ሒስትሪ ትምህርት ችግሮች

ትምርሕቱን በማስተማር ረገድ ዋናዎቹ እኔን የገጠሙኝ ችግሮች የዘዴ፣ ምርምርና ጥናትና የማስተማሪያ ማተሪያል ነበሩ፡፡ አሁን ስለነዚህ ለሜውታችሁ፡፡

### 4.1. ዘዴ

ስለማስተማሩ ዘዴ ለመወሰን መጀመሪያው ላይ ችግር ገጠመኝ፡፡ ትምርቱ እንደ ሌሎች የሕግ ትምህርቶች፤ ለምሳሌ የወንጀል፣ ፍትሐብሔርና ንግድ ወ.ዘ.ተ. ሕጎች ደረቅ ትምርት አይደለም፡፡ በዐይነቱና በወጥነቱ በአዋጅ ያለ ሕግ ደረቅ ነው፡፡ ሊጋል ሒስትሪ ሕግና ታሪክ የተዛመዱበት ነው፡፡

ለደረቅ ሕግ እላይ በሰጠሁት ምክንያት ሶክራቲክ ዘዴ መጠቀም ጥሩ ነው:: ኮንስትቲውሽናል ሎው በጠባዩ ከደረቅነት ይልቅ ወደ ስፋትና ሊጋል ሒስትሪ ቢቃረብም ለሱ ዲን ፖል እንዳረጋገጠው ሶክራቲክን ባመዛኙ መጠቀም ይቻላል:: ሶሶሎጂ አፍ ሎ በጠባዩ ለሊጋል ሒስትሪ በጣም ቅርበት አለው፤ እሱን ሳስተምር ተመሳሳይ ችግር ነበር የገጠመኝ::

እኔ እስከተረዳሁት ድረስ ታሪክን ለማስተማር ተመራጩ ዘዴ በአመዛኙ ሌክቸር ነው:: አልፎ አልፎ ጥያቄዎችና ዲስካሽን ይደረጋሉ ::

የነበረብኝ ውሳኔ የቱን ዘዴ ብጠቀም የሊጋል ሒስትሪን ዕውቀት፣ ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ለተማሪዎቹ አስተላልፋለሁ የሚል ነው:: በሊጋል ሒስትር ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ጥርጥር አልነበረኝም:: ታሪክን ያልተገነዘበ በታሪክ የተሰሩትን ስሕተቶች ይደግማል የተባለው ዋዛ አይደለም:: ታሪክ ደግሞ አሰስ ገሰሱና ተረት አይደለም:: የልጆች ማስፈራሪያ አይደለም::(ጅብ ይበላሃል ፖሊስ ጆሮህን ይቆርጣል እንደማለት::)

መጀመሪያ ሌክቸር እጠቀም ነበር:: በዚህም ተማሪዎቹ ስልቹ ሆኑ:: አንዳንዶቹ እንደውም ከትምህርቱ ይቀራሉ:: ከመጡትም አንዳንዶቹ ያንቀላፋሉ:: ከዚህም ውጪ ሌሎቹ ብዙዎች አፍጠው ማየት ነው እንጂ ተሳትፌ (ኢንተርአክቲቭ) አልነበሩም::ጥቂቶች ብቻ ፈራ ተባ እያሉ ይሳተፋ ነበሩ፤ ሊክቸሩንም ወደ ዲስካሽን ይወስዱት ነበር:: ከነዚህ ብዙዎቹ ዕድሜያቸውን ከርቸሌ (ወህኒ ቤት) ዩኒቨርስቲ ፈጅተው የመጡ ናቸው::

ከዛ በወቅቱ ከማስተምረው ዐቢይ አርዕስት አንድ ሃሳብ አነሳና ሌክቸር ሳይሆን ማብራሪያ ቢጤ እሰጥና ሶክራቲክ ዘዴ ጀመርኩ፤ እንደሁኔታው እሱን እተውና ወደ ዲስካሺን እገባለሁ:: ሁለቱን ዘዴዎች እያደባለቅሁ መጠቀም ከጀመርኩ በኋላ የተማሪዎቹ ተሳትፎ በጣም ጨመረ:: ከትምህርትም የሚቀሩ አልነበሩም:: ይህ ዘዴ የመጨረሻውን ሁኔታ ፈፀሚ ላረጋግጥ ባልችልም፣ ተማሪዎቹም እኔም ተጠቅመንበታል እላለሁ::

እስከቅርብ ጊዜ የቀድሞ ተማሪዎቼ፣ የአሁን ጓደኞቼ ስለ አንዳንድ ነገር እያነሱ ያጫውቱኝና ሲሞግቱኝ ብዙ ያላየሁትንና የረሳሁትን ያስታውሱኛል:: ይገርመኛል:: በወቅቱ የተማሪዎቹ ተሳትፎ በግልፅ ይታይ ነበር::

## 4.2. ሪሰርች

በእርግጥ ለሊጋል ሒስትሪ ብዙ ማንበብና ምርምር ማድረግ ነበረብኝ:: ያልሔድኩበት ቤተ መጻሕፍት አልነበረም:: ለምሳሌ ቤተ መጻሕፍት መመዘክር የቁም ፀሐፊና የአርካይቭ ክፍል ኃላፊ የነበሩ አቶ መላኩ ዘብሔረ ጉጃም በጣም ረዱኝ:: አንድ ቀን ደግሞ መነን ት/ቤት ቤተመጻሕፍት ቤት ሂጄ የጥንት መጽሐፎችና ሪፖርቶች አየሁ::

የኢትዮጵያ ሊጋል ሒስትር ለዚሁ ተብሎ ከተፃፏ መፅሐፎች የሚገኝ ሳይሆን ስለታሪክ፣ ሶሶዖለጂ፣ አንትሮፖለጂ ወ.ዘ.ተ. ጥናቶች ነው ያለው፡፡ በዚሁ ዐይነት የሪሰርች ሜዳ ሰፊ ስለነበር እንደ አበበ ቢቂላ /ምሩፅ ይፍጠር/ኃይሌ ገብረሥላሴ /ቀነኒሳ በቀለ/ደራርቱ ቱሉ/ጥሩነሽ ዲባባ/መሠረት ደፋር ሳንባ፣ ልብና ዊል ፖወር ይጠይቅ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ እንደዛ አይነት ሳንባ፣ ልብና ዊልፖወር ስለአልነበረኝ ሪሰርቹን አጠበብኩት፡፡

ከዚህ በተረፈ የፕራይማሪና ሴከንደሪ ምንጮች ትልቅ ችግር ነበር፡፡ በመሠረቱ የኢትዩጰያን ሊጋል ሒስትሪ ሶስት ክፍል አርገን ነው ማጥናት ያለብን፡፡ አንደኛ አክሱም-ክርስቲያን፣ ሁለተኛ ባህልና ልማድ የኦሮሞን ገዳ እንደምሳሌ ወስዶ እና ሶስተኛ እስላሚክ (ሸሪያ) ሕግ ግንኙነት ያለውን ባህልና ልማድ አገናዝቦ፡፡

እንግዲህ በዚህ ዐይነት የፕራይማሪና ሴከንደሪ ምንጮች የተዝረከረኩ ናቸው፡፡ የሚከተለውን እንደምሳሌ እንይ፡፡ ለአክሱም-ክርስትያን <u>ፍትሐ ነገሥት</u>፣ <u>ሥርዐተ ነገስት</u>፣ <u>መዋዕለ ነገሥት</u> (ክሮኒክል) እንደ ዋና የምንጭ ምሳሌ ይጠቀሳሉ፡፡ ለሁሉም ክፍሎች ሰከንደሪ ምንጮች በብዛት አሉ፡፡ የበጅ፣ ስቬን ሮብንሰን፣ ሥርግው ሀብለ ሥላል፣ ታደስ ታምራት፣ መርዕድ ወልደአረጋይ፣ ባሕሩ ዘውዴ፣ አስመሮም ለገሠ፣ ትሪሚንግሃም፣ ማርጃሪ ፐርሃም፣ ሃበርላንድ ጠቃሚ የሚባሉ ምንጮች ናቸው፡፡ <u>ዝክረ ነገር</u> ደግሞ በአብዛኛው ኘራይመሪ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካርዲናል የነበሩ አባ ጳውሎስ ፀዳዋ ወደ እንግሊዝኛ የተረጐሙት ከነመቅድምና የግርጌ ማስታወሻ <u>ፍትሐ ነገሥት</u> ተወዳዳሪ የማይገኝለት ኘራይመሪ ምንጭ ነው፡፡ በሌላ አንፃር ደግሞ የእንኮንቲ ሮሲን፣ ጊውዲ፣ ቼሩሊ ሰከንደሪና ኘራይመሪ ምንጮች አሉ፡፡

ይህ ሁሉ ቢኖርም ማነፃፀርና መጭመቅ የግድ ነው፡፡ ድካሙ ሁሉ እዚህ ላይ ነው፡፡ ሰከንደሪው ወደኘራይማሪ ሲጠቁም፤ ኘራይመሪው ደብዙ ሲጠፋ አስቸጋሪውና ተስፋ አስቆራጩ ይህ ነው፡፡ በዚህ ዐይነት ነበር የማስተማሪያ መጽሐፍ ሳዘጋጅ <u>ያለምኩትና</u> ያቀድኩት፡፡

### 4.3 የማስተማሪያው ማቴሪያል

ይህን ለማዘጋጀት ስማስን ብዙ ተማርኩ፡፡ ተማሪዎችን ከፉም ለማ በግርድፍ የተዘጋጀው ማተሪያል ምን ያህል ጠቅሞ ይሆን ዛሬም የምጠይቀው ጥያቄ ነው፡፡ የሚቆጨኝ እሱን በደንብ አስተካክዬ፣ በኢሹ፣ ጥያቄና መልስና ማብራሪያ እየሰጠሁ እያረምኩ እሰራዋለሁ ስል ዘመኔን ረስቸው ጥሩተኛ ተብዬ ጡረታ ወጣሁ፡፡ ከዛ እሱም ጥሩተኛ እኔም ወደ ቀረኝ ዘመን አኗኗር ተዛወርኩ፡፡

በየምክንያቱ አንዳንድ ሰዎች ስለማቴሪያሉ ሲያነሱብኝ፣ ለምሳሌ መምህራን ኤልያስ ኑርና ሙራዱ፣ ካለበት አወጣና አቧራውን አራግፌ ሳገላብጠው ጭራሹን ተስፋው ጭልም ይላል፡፡ችግሩ በአሁኑ ወቅት የተቀነሰ ቢመስልም ዋና ዋናው

ችግር እንዳለ ነው፡፡ ያንን ለመቋቋም የኔ ሁኔታና ዕድሜ የሚችለው አይመስለኝም፡፡ አሁን የሚያጓጓና ብርታት የሚጋብዝ የተስፋ ሁኔታዎች ያን ጊዜ ቢኖሩ ምንኛ በተሰራ፡፡

እንግዲህ ችግሮቹ ምንም ይሁኑ ምንም መፍትሔው ያለው እኔ ዘንድ አይመስለኝም፡፡ እንደተባለው ሴትየዋ ልጇ ጠፋ ብላ «ያገር ያለህ! አገር ይታሰስልኝ ...” ብላ ጮኸች አሉ፡፡ ጎረቤትዋ የሆነ ሰው “አገር ለምን ይታሰሳል! እንዴትስ እርጎ ይሰማ አንቺ እየጨህሽበት፤” አላት ይላሉ፡፡ ወጣ ወረደ የሚከተለው ስለማቴሪያሉ ሁኔታ በአጭሩ ሳያስረዳ አይቀርም ብዬ አምናለሁ፡፡

የማቴሪያሉን ቴብል ኦቭ ኮንቴንት (አርዕስት ማውጫ) ያየ ምኞታዊና ሐሳባዊ ነው ቢል እውነቱን ነው፤ በዛ መንፈስና ስሜት ነበር ያዘጋጀሁት፡፡ በሱ መሠረት እንደማላስተምርና ማተሪያሉንም ጨርሼ እንደማላዘጋጀው አውቀው ነበር፡፡ ፕላን ማውጣቴ ነበር፡፡

ቴክስቶቹ ወጥ ሳይሆኑ እንደ የአርእስቱና ምዕራፉ የቀረቡ ነበሩ፡፡ የመጀመሪያ መግቢያ ምዕራፎች ቴክስቶች (ለምሳሌ) ስለ ጥንታዊ ሕግ ሚስፖታሚያ፣ ግሪክ እና ሮማን ሲሆን፣ ኢሹ እያወጣሁ ጥያቄና መልስ እያደረግሁ ነበር፡፡ ማለት ልክ እንደ አሜሪካን ሎ ስኩል ማስተማሪያ ማተሪያል፡፡ ይህ አድካሚና ጊዜ የሚወስድ ሆነ፤ ማስተማሩንም ሊጎትትብኝ ሆነ፡፡ እሱን ወደፊት የሥራ ቀጠሮ ሰጠሁና የቴክስቶች ተዋፅኦ ማውጣት ጀመርኩ፡፡ ለምሳሌ ስለታሪክ ካር (እኔን ከ ቶይን ቢ ይልቅ ያስደነቀኝ ብዙ ተማሪዎቼም ተደናቂ ሆነዋል)፣ ባርኩን ስለ ሊጋል ሒስትሪ ምንነትና ኢንተርዲሲፕሊነሪ አቀራረብ፣ ስለ ሕግ ሶሶዎሎጂ፣ ሐዛርድ የራሻን ሕግ ሐዛርድ በ ሞስኮ የተማረ አሜሪካዊ ሲሆን ሃርቫርድ ያስተማረ በራሻ ሕግ ኤክሰፐርት ነበር፡፡ እላይ ያነሳሁት የስታንፎርድ ፕሮፌሰር በቻይና ሕግ ከዚያ ስለኢትዩጵያ፡፡ በነገራችን ላይ በደርግ ዘመነ መንግሥት ስለ ማርክዚም ሌሊንዝም ትምህርትና የማስተማር ዘዴ ከዋናው ወንዝ እንድንጠመቅ ታዘን ሞስኮ በሔንድንበት ወቅት የሌኒን ዩኒቨርስቲ ፋኩልቲዎችን እንደናይና አስተማሪዎችንም እንድናነጋግር በጠየቅነው መሠረት ሕግ ትምህርት ቤትን ስንጎበኝ በዓለም አቀፍ ታዋቂ የነበረውና የዓለም አቀፍ ሕግ ኤክስፐርት የሆነውን ፕሮፌሰር ቶንኪንን ስናነጋግር ስለ ራሺያ ዩኒ ሲስተም ስጠይቀው ምዕራባዊ ነው እንደኢሮፕ ነው ብዙ ኢሮፒያንና አሜሪካኖች የፃፉትን እንጠቀማለን ብሎኛል ፤ በተለይ ሐዛርድን ጠቅሶ ይታያችሁ ማተሪያሉን በማዘጋጅበት ወቅት ሪሰርች ወጪ እና አሲስታንት ብሎ ነገር የለም፤ ጣርና ጋር፤ማሰን ብቻ ነበር፡፡ እነ ሎዊንሽታይንና ሴድለር ወጪና ረዳቶች ነበርዋቸው፡፡ ታዲያ ምን ይባላል፡፡ ለማንኛውም ከሞላ ጎደል ማተሪያሉ አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ በተለይ የኋላ ተማሪዎች የአሁን ተማሪዎችም በአጋጣሚ ስንገናኝ እንደተጠቀሙበት ነግረውኛል፡፡

ሥራው ግን በጣም ፈታኝና አድካሚ ነበር፡፡ ሶስት አራት ጊዜ መከለስና መሻሻል ነበረበት፡፡ አሜሪካ አገር የሎ ስኩል አስተማሪዎች ማተሪያል የሚያዘጋጁት

በቀላሉ ወደ 20 ዓመት ካስተማሩ በኋላ ነው፡፡ ስለሆነም ፍሮይንድ የታወቀ አስተማሪና የሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር- Teaching Material አልነበረውም፡፡ የሚነበቡ መጻሕፍት ብቻ ይጠቁማል፡፡ እንዲሁም ስዘርላንድ፡፡ አቅትዋቸው ሳይሆን ምክንያት ነበራቸው፡፡ የሳክስ Legal Process በኔ ጊዜ ያልታተመ ረቂቅ ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ በነሱ ደረጃ ነው፡፡ የኛ ደረጃና ችግር ደግሞ እራሱን የቻለ ነው፡፡ በተለይ አሜሪካኖቹ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን አስረክበው ከሔዱ በኋላ የሪሰርች ጉዳይ አከተመ ጆርናሉ ስንት ጊዜ ካቆመ በኋላ ነው የታተመው፡፡ እዚህ ላይ አጥብቄ ላሳስብ የሞከርኩት የነበረውን ችግር እንጂ የማተሪያሉን ስሕተት፣ ውሱንነትና ድክመት ለመካድ አደለም፤ ለመሸፈን አደለም፣ ለማድበስበስም አደለም፣ ብዙ ስሕተቶችና ድክመቶች አሉበት፡፡

## 5. መዝጊያ

ከዕለታት አንድ ቀን ፒያሳ ጫማ አስጠርግ ነበር፡፡ አጠገቡ የጥላሁን ገሠሠ ዘፈን ምድርና ሰማይ እያደባለቀ ከሙዚቃ ቤት ተለቋል፡፡ ሊስትሮው እቀመጥበታለሁ አለ በድንገት ግርም አለኝና፣ "ምኑን?" አልኩት፡፡ "የምን ታረጊዋለሽን?ችግር፣" አለኝ፡፡ ዘፈኑ ውስጥ "ምን ታረጊዋለሽ?ምን ታረጊዋለሽ?" የሚል ስንኝ ነበር፡፡ ጫማዬን አስጠርጌ የሌስትሮውን አነጋገር እያሰላሰልኩኝና ብቻዬን እየሳቅሁ ተነስቼ ሔድኩ፡፡ አሁንም እቀመጥበታለሁ፡፡ አሜን፡፡